31ኛ ዓመት ቁጥር 205
አሶሳ፣
የካቲት/ 2017 ዓ.ም

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
# ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ፣

LISAN HIG-GAZETA

Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት**

**ጠባባቂነት የወጣ**

ፖ.ሳ.ቁ. 293
ያንዱ ዋጋ------------

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 205/2017

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ፍ/ቤቶች በህግ የበላይነት፣ በግልጽነትና በተጠያቂነት መርሆች ላይ የተመሰረተ ቀልጣፋ፣ ዉጤታማና ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ይበልጥ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

የክልሉን ፍ/ቤቶች አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያት የወጡትን የማሻሻያ አዋጆች ከለዉጥ ስራዎች ከፍርድ ቤቶች ፍኖተካርታ እና አዳዲስ ሀሳቦች ጋር በማጣጣም መከለስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የዳኝነት ሥርዓቱን ለማጠናከር የክልሉ ፍርድ ቤቶች በበጀት ምደባና በአስተዳደር ራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን የሕግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 163/2011 በተደጋጋሚ መሻሻሉ ለአሰራር አመቺ ባለመሆኑና በተሻሻለ አዋጅ መተካት ስላስፈለገ፤

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ (49(1) እና 3 (1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 205/**2017** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1 "ጠቅላይ ፍርድ ቤት" ማለት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ነዉ::

2 "ከፍተኛ ፍርድ ቤት" ማለት የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማለት ነው፡፡

3 "ወረዳ ፍርድ ቤት" ማለት በዞን ስር ባሉ ወረዳዎች፣በልዩ ወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ክልል የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥ ፍ/ቤት ማለት ነዉ፡፡

4 "ዳኛ" ማለት በህግ አግባብ፣ በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተመርጦ በክልሉ ምክር ቤት የተሾመ የተፈጥሮ ሰዉ ነው፡፡

5 "ምክር ቤት" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ማለት ነው፡፡

6 "መንግስት" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማለት ነው፡፡

7 "ጉባዔ" ማለት የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማለት ነው፡፡

8 "መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት" ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት ያለበትን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25-26 መሰረት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊታይ የሚችልን የመጨረሻ ዉሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን፣ትእዛዝ፣ ያጠቃልላል፡፡

(ሀ) የፌደራልም ሆነ የክልል የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን

(ለ) ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሕግ የሚጠቅስ፣

(ሐ) ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤

(መ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፤

(ሠ) በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፤

(ረ) ጉዳዮን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ ፤

(ሰ) የአስተዳደር አካል ወይም የሸርዓ ችሎት ወይም የማህበራዊ ፍ/ቤት ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠው ውሳኔ፣

(ሸ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በሚቃረን የተሰጠ ዉሳኔ ፡

7) **"የመጨረሻ ውሳኔ"** ማለት በፍርድ ቤት ፣ በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል፣ በተቋማት ወይም በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች የተሰጠ እና ለጉዳዩ እልባት የሚሰጥ ፍርድ ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ፣ ውሳኔ ወይም የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ ፍርድ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔን ይጨምራል፡፡

9) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠዉ ሰዉ ነዉ፡፡

10) በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸዉ የሴትንም ጾታ ያጠቃልላል፡፡

## አንቀጽ 3. ስለ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 78/3/ እና የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቋቋሙ ሆኖ አደረጃጀቱ የሚከተለዉ ይሆናል፡፡

1 የጠቅላይ ፍርድ ቤት

2 የከፍተኛ ፍርድ ቤት

3 የወረዳ ፍርድ ቤት

በየደረጃ ያሉ ፍ/ቤቶች ኘሬዚዳንት፣ ምክትል ኘሬዝዳንት፣ እንዲሁም የዳኝነት ስራዉን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ፣የስራ ሂደት ባለቤቶች፣ አስተባባሪዎች፣ ሪጅስትራሮች ፣ተከላካይ ጠበቆች እና እንዲሁም በጠ/ፍ/ቤት ደረጃ የዳኞች አስተዳደር ጉበኤ ጽ/ ቤት ኃላፊ ፣በዳኝነት ማእረግ የተሸሙ ባለሙያዎች፣ እና ዳሮክትሬቶች ሌሎች የአስተዳደር ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የክልል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን

### አንቀጽ 4.መሠረት

1 ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሕግ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር በክልሉ ሥር ባሉት ጉዳዮች የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

2 በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ሥር መታየት ሲገባቸው ለክልሉ ፍ/ቤቶች በውክልና የሚሰጡትን ጉዳዮች የመዳኘት ሥልጣን አላቸው፡፡

3 የክልሉ ፍርድ ቤቶች ከክልሉ ህገ-መንግስት ጋር የማይጣጣም ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ የመሻር ሥልጣን አላቸው፡፡

4 በውክልና መሠረት በሚታዩ የፌዴራል ጉዳዮች እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ክልላዊ ጉዳዮች በስተቀር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 5. ተግባራዊ የሚሆኑ ሌሎች ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጋጩ በስራ ላይ ያሉ የፍትሐብሔርና የወንጀል ሕጉች ከነ ሥነ-ሥርዓታቸው እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጉች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለዳኝነት ስልጣን

### አንቀጽ 6. የጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

1 ጠቅላይ ፍ/ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ/ ከከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡለትን የይግባኝ አቤቱታዎች አይቶ ይወስናል፡፡

ለ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ እንዲሁም የከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የወረዳ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ የተለየ የሰጠበትን ጉዳይ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ሐ የዚህ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) እንደተጠበቀ ሁኖ በወንጀል ጉዳይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከወረዳ ፍርድ ቤት የተለየ ውሣኔ ባይሰጥም በይግባኝ የማየት ስልጣን አለዉ ፡፡

መ/ በሥነ-ሥርዓት ሕግ በተወሰነው መሠረት አንድ ጉዳይ ከአንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ጥያቄ ሲቀርብለት ውሣኔ ይሰጣል፡፡

ሠ/ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትንና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ክልላዊ

ጉዳይ በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ረ/ በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዩ የፌደራል ጉዳዮችን በይግባኝ ማየት ስልጣን አለዉ፡፡

ሰ/ አንድን ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ወይም ወረዳ ፍ/ቤቶች ሥልጣናችን ነው ብለው የያዙት ወይም ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ በጉዳዩ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በሚቀርብ ጥያቄ፣አይቶ መወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 7. የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን

1. ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ/ በፍትሐብሔር እና በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህጐች እና በሌሎች ህጎች ውስጥ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲያያቸው የተዘረዘሩት ጉዳዮች፣እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. በሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ግምታቸዉ ብር 500,000/አምስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ የሚሆኑ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን
2. በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ግምታቸዉ ከብር 1,000,000 /አንድ ሚልዮን ብር/ በላይ የሚሆኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የማየት ስልጣን አለዉ፡፡

ለ/ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ሥር በሚወድቁና በውክልና በተሰጡ ጉዳዮች፣

ሐ/ አንድ ጉዳይ ከሥሩ ካሉ የወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ፣

መ/ አንድን ጉዳይ በሥሩ ካሉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የወረዳ ፍርድ ቤቶች ሥልጣናችን ነው ብለው የያዙት ወይም ስልጣናችን አይደለም ብሎ የመለሱት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ ተገቢው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን አለው፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1_ሐ/ እና /መ/መሠረት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የሚሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ አይኖረውም፡፡

3. ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከወረዳ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚቀርብለትን ጉዳይ አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው

## አንቀጽ 8.የወረዳ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን

በሕጉ መሠረት ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡-

1. በፍትሐብሔርና ወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጐች እና በሌሎች ሕጐች ውስጥ በወረዳ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነዉ፣

ሀ. በሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ግምታቸዉ እስከ ብር 500,000/አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሚሆኑ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን

ለ. በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ግምታቸዉ እስከ ብር 1,000,000 /አንድ ሚልዮን ብር/በሚሆኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የማየት ስልጣን አለዉ፡፡

2. ከማኀበራዊ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን አለው፡፡

3. የአካል ነጻነት ፣ አባትነት ይረጋገጥልኝ እና በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ጉዳዮች በሚቀርቡ አቤቱታዎች አይቶ የመወሰን ስልጣን አለዉ፡፡

## ክፍል አራት

## የፍርድ ቤት ኃላፊዎች ስልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 9. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘረዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉን የዳኝነት አካል ይወክላል፣
2. የፍርድ ቤቶችን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
3. በዳኞች የአስተዳደር ጉባኤ እስኪሾም ረዳት ዳኛ መድቦ የማሰራት ስልጣን አለዉ፡፡
4. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን በየችሎቱ ይደለድላል፤ በዳኞች የዓመት ዕረፍት ጊዜ ለተረኛ ችሎት ዳኞችን ይመድባል፣ ዳኞችን፣ሬጅስትራሮችንና ተከላካይ ጠበቆችን ያስተዳድራል፣
5. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባዔ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፣ይመራል፤
6. አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤትን በሚመለከት ረቂቅ ህግ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
7. ስለ ክልሉ ፍርድ ቤቶች የሥራ ክንውን ሪፖርት ለምክር ቤት ያቀርባል፣
8. የሕግ መጽሔትና የፍርዶች መጽሐፍ እንዲታተም ያደርጋል፡፡
9. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
10. የፌደራሉ ሆነ የክልል መንግስታት ያወጡዋቸዉን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉስጥ ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል ያረጋግጣል፤
11. በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በመልካም ስነ-ምግባር የታነጹ ስለመሆናቸዉ በቅርብ ይከታተላል ያረጋግጣል፤

12. የክልል ፍ/ቤቶች የስራ አፈጻጸም ቀልጣፋና ዉጤታማ ለማድረግ የሚረዱ አዳዲስ አሰራር ስልቶች ይቀይሳል ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል፤
13. በክልሉ ዉስጥ የዳኝነት ስራ ለማጠናከር ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ይሰራል፤
14. በዳኞች ሆነ በሌሎች የክልሉ መንግስታት ባለስልጣናት ሹመት አሰጣጥ ስነ ስርዓት ላይ ተገኝቶ ቃለ መሃላ ያስፈጽማል፤
15. የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ጉዳይ በውክልና ለሚሠሩ ፍ/ቤቶች የበጀት ማካካሻ ከፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
16. የክልሉን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡
17. የፍርድ መዛግብት አያያዝና አጠቃቀም የሚሻሻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
18. ዳኞችና ሠራተኞች ትምህርትና ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
19. በህግ መሠረት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 10.<u>የምክትል ኘሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር</u>

የጠ/ፍ/ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለጠ/ፍ/ቤቱ ኘሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-.

1.በፕሬዝደንቱ ተለይተዉ የተሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፤

2.ፕሬዝደንቱ በማይኖርበት ወይም ስራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፤

## አንቀጽ 11. <u>ስለጠቅላይ ፍርድ ቤትፕሬዝደንት እና ምክትል ፕሬዝደንት ከኃለፊነት መነሳት፣</u>

**1.የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ወይም ምክትል ፕሬዝደንት ስራዉን ሊለቅ ወይም ከኃላፊነት ሊነሳ የሚችለዉ በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ ሲወስን፣ ጥፋት ሲፈጸም ወይም በአመራር ረገድ ጉልህ ድክመት ማሳየቱ ሲታመን ነዉ፡፡**

2. . በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ1 ስር የሰፈረዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በራሳቸዉ ፈቃድ ስራዉን ለመልቀቅ ከወሰነ ከመልቀቁ 3 ወር አስቀድሞ ለርእሰ መስተዳድሩ በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

3. የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ወይም ምክትል ፕሬዝደንት በራሳቸዉ ፈቃድ ከኃላፊነት ሲነሱ በዳኝነት ስራ ጋር በተያያዘ ጥፋት እስካልፈፀሙ ድረስ ዳኛ ሁኖ መስራት አይከለከሉም፡፡

### አንቀጽ 12. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. ፍርድ ቤቱንና በሥሩ ያሉትን የወረዳ ፍርድ ቤቶች ይወክላል፣
2. የፍርድ ቤቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለጠ/ፍ/ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ የፍርድ ቤቱን ዳኞችን በየችሎቱ ይደለድላል፣
3. በዳኞች አመት እረፍት ጊዜ ለተረኛ ችሎት ዳኛን ወይም ዳኞችን ይመድባል፡፡ ሬጅስትራሮችንና ተከላካይ ጠበቆችን ያስተዳድራል፡፡
4. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የፍርድ ቤቱን፣ ሠራተኞች፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል ፡፡

6. ስለፍርድ ቤቶች የሥራ ክንውንና በየ3 ወሩ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

7..ትምህርታዊ የሆኑ ፍርዶችና ውሣኔዎችን ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይልካል፣

8. በህጉ መሠረት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

### አንቀጽ 13. የወረዳ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር

የወረዳ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ኘሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡ፍርድ ቤቱን ይወክላል፡፡

1. ዳኞችን በየችሎቱ ይደለድላል፣በዳኞች የአመት እረፍት ጊዜ ለተረኛ ችሎት ዳኞችን ይመድባል፣ሪጅስትራሮችን እና ተከላካይ ጠበቆችን ያስተዳድራል፣
2. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ያሰናብታል፣
3. የፍርድ ቤቱን እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀርባል፣ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. ስለ ፍርድ ቤቶች የሥራ ክንውንና ስታትስቲክስ በየ3 ወሩ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ፣ ለከፍ/ፍ/ቤትና ለወረዳው ም/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣

5 በሕጉ መሠረት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

### አንቀጽ 14.የዋና ስራ ሂደት ዳሮክተሮች ስልጣንና ተግባር

በየደረጃ ባሉ ፍ/ቤቶች የሚገኘዉና ከችሎት ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ተግባራት የሚመራ ዋና የስራ ሂደት ዳሮክተር በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩቱል፤-

1. የሂደቱን የመግባቢያ ሰነድ ወይም ቲም ቻርተር ከሂደቱ አባላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤
2. የስራ ሂደቱ ዕቅድ ያዘጋጃል ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል ሲጠየቅም የስራ ሪፖርት

ያቀርባል፤

3. ለእያንዳነዱ የሂደቱ አባል የስራ ስምሪት በመስጠት በተቀመጠዉ የጉዳዮች እስታንዳርድ መሰረት አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
4. የሂደቱን ስራዎች በባላይነት ያስተባብራል ድጋፍ ይሰጣል፤
5. ጠንካራና ደካማ አፈጻጸም በመለየት ችግር ፈቺ በሆኑ ሐሳቦች ላይ የሂደቱን አባላት ያወያያል የመዝገቦች ብዛትና ፍሰት እያጠና የተሻለ የአሰራር ስርዓት እንዲዘርጋ ለፍ/ቤቱ የስራ ኃላፊ ሃሳብ ያቀርባል፤
6. አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ሂደቱን በመወከል በተለያዩ ስብሰባዎች ይካፈላል፤
7. የሂደቱን ተግባራት በወጣላቸዉ ቅደም ተከተል መሰረት መፈጸማቸዉን ያረጋግጣል፡፡
8. በሂደቱ ስር በሚገኙ ችሎቶች የሚያስችሉ ዳኞች ተሟልተዉ ማስቻላቸዉንና ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ መወጣታቸዉን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
9. ከባለጉዳዮች በኩል የሚቀርቡና ከመዛግብት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ አቤቱታዎችን ይቀበላል እንደ አስፈላጊነቱ መፍትሔ ይሰጣል ወይም ጉዳዩን ለሚመለከተዉ ያስተላልፋል፤
10. በፍ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናዉናል፤

## አንቀጽ15.<u>የሪጅስትራር ሥልጣንና ተግባር</u>

በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ሪጅስትራር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በፍትሐብሔርና በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጎች መሠረት ለችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ያጣራል ይመረምራል፣
2. በችሎት የሚሰጡ ትእዛዞችንና ዉሳኔዎችን ለሚመለከታቸዉ አካላት ያስተላልፋል፡፡
3. ከባለጉዳይ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀብሎ ያጣራል እንደ አግባብነቱ ለሚመለከተዉ አካል ይመራል ምላሽ ይሰጣል፡፡
4. በሥሩ ያሉትን ሠራተኞች ያስተባብራል ይቆጣጠራል፡፡
5. ከኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ16. <u>የተከላካይ ጠበቃ ተደራሽነትና ሥልጣንና ተግባር</u>

ሰብአዊ መብት ከማስከበር አንጻር በአሁኑ ሰዓት በከፍ/ፍ/ቤት በጠ/ፍ/ቤት ደረጃ ብቻ ተወስኖ ያለዉ ጠበቃ መድቦ ማሰራት እንደሁኔታዉ ታይቶ በወረዳ ፍ/ቤት ላይም ተደረሽ ይሆናል፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ተከላካይ ጠበቃ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ከመንግስት ጠበቃ እንዲቆምላቸው በችሎት ለታዘዘላቸው ተከሣሾች የሕግ ምክር አገልግሎት ይሰጣል ይከራከርላቸዋል፡፡
2. ተከሳሽን እያማከረ በችሎት በሚሰጥ ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ ቅሬታ ሲኖረዉ በህጉ መሰረት ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ በማቅረብ ይከራከራል፡፡
3. ስለ ሥራው ወቅታዊ ሪፖርት ለኃላፊው ያቀርባል፡፡
4. ከኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 17 የፍርድ አፈጻጸም ባለሙያ ተደራሽነትና ስልጣንና ተግባር

1. በየትኛዉ ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ባለሙያ ሊመደብ ይችላል፡፡
2. በማንኛዉም ጉዳይ በፍ/ቤት በዳኝነት የተሰጡ ትእዛዞች፣ ዉሳኔዎች፣ቅጣቶች እንዲያስፈጽም ሲታዘዝ ያስፈጽማል፡፡
3. ስለ ሥራው ወቅታዊ ሪፖርት ለኃላፊው ያቀርባል፡፡
4. ከኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## አንቀጽ 18. ስለማስቻያ ሥፍራ

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስቻያ ሥፍራ የክልሉ ዋና ከተማ ይሆናል፡፡
2. የከፍተኛ ፍርድ ቤት የማስቻያ ሥፍራ በዞኑ ከተማ ይሆናል፡፡
3. የወረዳ ፍርድ ቤት ማስቻያ ሥፍራ በወረዳው ከተማ ይሆናል፣፣
4. የከተማ ፍ/ቤት የሚያስተናግዳቸዉ ጉዳዮች በከተማዉ የክልል ወሰን ዉስጥ በሚቀርቡ የወንጀልና የፍ/ር ጉዳዮች ሆኖ ማስቻያ ስፍራዉ ከተማ አስተዳደሩ በተቋቋመበት ከተማ ይሆናል ፡
5. መደበኛ የማስቻያ ሥፍራ እንደተጠበቀ ሆኖ በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ ፍርድ ቤት ለቀልጣፋና ለተደራሽነት የፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊነቱን ሲያምንበት ዳኛው ወይም ዳኞችን በመላክ በሥልጣኑ ክልል ውስጥ በየትኛውም ሥፍራ ተንቀሳቅሶ ሊያስችል ይችላል፡፡

## አንቀጽ19.የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

1. የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 6 ( 1) መሠረት የስራ ቋንቋው አማርኛ ነው፡፡
2. ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋውን ለማይችል ባለጉዳይ አስተርጓሚ ይመድባሉ፡፡

## አንቀጽ 20. ስለ ፍርድ ቤት ችሎቶች

1. ማንኛውም ፍርድ ቤት የፍትሐብሔርና የወንጀል ችሎቶች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ችሎቶች ይኖሩታል፡፡
2. በእያንዳንዱ የጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎቶች አንድ ሰብሣቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ፡፡
3. የጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ም/ኘሬዚዳንት ማንኛውንም የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት፣በተመሳሳይ ሁኔታም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ማንኛውም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት ሊሰበስብ ይችላሉ፡፡
4. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ሰብሳቢ ወይም ዳኛ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት ዳኛ ሲጓደል አሟልቶ ያስችላል፡፡
6. በዳኞች የአመት ዕረፍት ጊዜ ተረኛ ችሎት ይኖራል፡፡
7. የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ ወይም ኘሬዚዳንት ከከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ ሲጓደል አሟልቶ ያስችላል፡፡
8. የወረዳ ፍ/ቤቶች ችሎቶች በአንድ ዳኛ ያስችላሉ፡፡

## አንቀጽ 21. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል፡፡

1. ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆኑ ችሎቶች ያስችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለዳኝነት አሠራር አግባብ ያላቸው ሥነ-ሥርዓት ሕጐች የተጠቀሰው እንደተጠበቁ ሆነዉ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ፍርድ ቤቶች በዝግ ችሎት ያስችላሉ፡-

ሀ/ ለተከራካሪዎች የግል ህይወት

ለ/ ለሕዝብ እና ለመንግስት ሰላምና ፀጥታ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም

ሐ/ ለሕዝብ መልካም ፀበይ ወይም ግብረገብነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ

መ/ ህጻናት ተከሰዉ ወይም ምስክር ሁነዉ ሲቀርቡ ፍ/ቤቶች በዝግ ችሎት ያስችላሉ፤

## አንቀጽ 22. ጠበቃ ስለማቆም

1. ማንኛውም ሰው ተከላካይ ጠበቃ የማቆም መብት አለው፡፡
2. ጠበቃ ማቆም ለማይችል ተከሣሽ ፍትህ ሊጓደል የሚችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግስት ተከላካይ ጠበቃ ይመድብለታል፡፡

## አንቀጽ 23. ዳኞችን ከችሎት ስለማንሣት

**1. ማንኛውም ዳኛ ከችሎት የሚነሣው፡-**

ሀ/ ከተከራካሪዎቹ ወይም ከጠበቃው ጋር በክልሉ የቤተሰብ ህግ እንደተደነገገው የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ወይም ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ሚስቱ ወይም ሞግዚቱ ወይም ሕጋዊ ወኪል ወይም ጠበቃ በሚሆንበት ነገር ላይ ክርክር የተነሣ እንደሆነ፣

ለ/ ክርክር የተነሣበትን ነገር አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በዕርቅ መንገድ የያው እንደሆነ፣

ሐ/ ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ውስጥ ከአንደኛው ጋር ሙግት ወይም ጸብ ያለው እንደሆነ፣

2. ማንኛውም ዳኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተገለጸውን ሁኔታ እንዳወቀ ከችሎቱ መነሣት ይኖርበታል፡፡
3. ዳኛው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ / 2/ መሠረት ከችሎት ካልተነሣ ማመልከቻ የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ  በሌለበት ሌሎች ዳኞች ማመልከቻውን መርምረው የሚሰጡት ዉሣኔ ይግባኝ የሌለው የመጨረሻው ውሣኔ ይሆናል፡፡
5. አንድ ዳኛ በሚያስችልበት ችሎት  ከዳኝነት ይነሳልኝ አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዩ እንዲወሰን ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማስተላለፍ አለበት፤
6. ያለበቂ ምክንያት ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ ማመልከቻውን ባቀረበው ተከራካሪ ወገን ላይ አቤቱታውን የመረመሩት ዳኞች ከአንድ ሺህ እስከ ሶስት ሺህ ብር መቀጮ ሊጥሉበት ይችላሉ፡፡
7. በዚሁ አዋጅ መሠረት ዳኛው ከችሎት እንዲነሣ የሚቀርብ ማመልከቻ ያስከተለው ኪሣራ ከዋናው ነገር ኪሣራ ጋር ይጠቃለላል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ተገቢ አይደለም በማለት ሣይቀበለው ከቀረ የዋናውን ነገር ውጤት ሣይመለከት ኪሣራውን የሚከፍለው ማመልከቻውን ያቀረበው ሰው ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 24. ውሣኔ አሰጣጥ

1. ዳኞች በአንድ ችሎት ከአንድ በላይ  ሆነው በሚያስችሉበት ጊዜ በውሣኔ አሰጣጥ ላይ የሐሳብ ልዩነት ካላቸው የአብዛኛው ድምጽ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በመዝገቡ መስፈር አለበት፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ከአምስት ያላነሱ ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት</u>

## አንቀጽ 25. <u>የሰበር ሰሚ ችሎት</u>

1. በክልሉ አንድ የሰበር ሰሚ ችሎት ተቋቁሞ ለሰበር የሚቀርቡ ጉዳዮች ያያል፡፡

2. የሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት የማያንሱ ከሰባት የማይበልጡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት ነው፡፡

3. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ኘሬዚዳንት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 26. <u>የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት</u>

1. በአንድ ጉዳይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ሊታይ የሚችለዉ ጉዳዩ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሶሶት ዳኞች ለሚሰየሙበት አጣሪ ችሎት ከቀረበና ችሎቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብለዉ ያመኑ እንደሆነ፣
2. ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ ጉዳይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት በማመልከቻው ላይ በዝርዝር ጽፎ ማቅረብ አለበት
3. አቤት ባዩ ከማመልከቻው በተጨማሪ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔና የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅጂዎችን ማቅረብ አለበት፣
4. የሰበር ማመልከቻ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዲይ ሊይ የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጠ በዘጠና ቀን ውስጥ ይሆናል ሆኖም በልዩ ሁኔታ በበቂ ምክንያ ችሎቱ ካመነ ከሶስት ወር በኃላም ጉዳዩን ማየት ይቻላል ፡፡

## አንቀጽ 27. የክልል ፍርድ ቤቶች የስራ ጊዜ

1) የክልል ፍርድ ቤት ዳኞችና እና ሰራተኞች የስራ ሰዓት ከሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች የስራ ሰዓት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ ቢኖርም የክልል ፍርድ ቤቶች በየአመቱ ከነሐሴ 1 እስከ መስከረም 24 ድረስ በከፊል ዝግ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 28. <u>የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር</u>

1. የክልሉ ፍ/ቤቶች የሚቀርቡላቸዉን ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ወይም የሚጠናቀቁበትን የጊዜ ሰሌዳ ገደብ በማስቀመጥ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ የተሳለጠ እና ጥራቱ የሚረጋገጥበት የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ተግባራዊ ያደርጋሉ ፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 የተገለጸዉን ለማስፈጸም ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

### አንቀጽ 29. በቴክኖሎጅ የተደገፈ የመዝገብ አመራር ስርአት ስለመዘርጋት

1) የክልል ፍርድ ቤቶች በማንኛዉም የፍርድ ቤት ደረጃ የሚቀርቡ የፍታብሄር ወይም የወንጀል ጉዳይ ክርክሮች አዳዲስ የመረጃ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ዳጂታል ወይም አዉቶሜትድ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ስርዓት ሊዘረጉ ይችላሉ፡፡

2) ተከራካሪ ወገኖች በተዘረጋዉ ስርኣት መሰረት ክርክሮቻቸዉን የማካሄድ ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ዝርዝሩ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 30. የፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትዕዛዞች

1) በማንኛውም የክልል ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በህግ እስካልተለወጠ ድረስ የፀና ሆኖ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) የክልል ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸዉን ዉሳኔዎች ወይም ተእዛዞች በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ዉስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ በማንኛዉም በክልሉ ሴክተር፣ ዞንና ወረዳ ዉስጥ የሚገኝ የመንግስት አካል፣ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ማንኛዉም ሰው ውሳኔዎቹን ወይም ትእዛዞቹን የመፈጸም እና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

3) ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ የማይወጣ ከሆነ በዚህ አዋጅና አግባብ ባለው ሌላ ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 31. ቅጣት፣

1) የፍርድ ቤት ወይም የዳኞችን በነጻነት መስራት የሚጋፋ ወይም በዳኞች ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ወይም ለማድረግ የሞከረ ማንኛው ሰዉ በሌላ ህግ ከፍ ያለ ቅጣት ከሌለ በቀር ከሦስት ወር እሥራት ባላነሰ ከሁለት አመት ባላበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡፡፡

2) የፍርድ ቤትን ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ የማይፈጽም ወይም ለመፈጸም መሰናክል የሚፈጥር ወይም ሲጠየቅ ለመፈጸም ተባባሪ የማይሆን ማንኛዉም ሰዉ በሌላ ህግ ከፍ ያለ ቅጣት ከሌለ በቀር ከሁለት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል

## ክፍል ሰባት

## ስለ ክልል ፍርድ ቤቶች በጀትና የሰው ሀብት አስተዳደር

## አንቀጽ 32. የክልል ፍ/ቤቶች የበጀት አስተዳደር ነፃነት

1) የክልል ፍ/ቤቶች ከመንግሥት በጀት ላይ ጥቅል የሆነ የፍርድ ቤት ፈንድ ይመደብላቸዋል፡፡

2) የሚመደበው ጥቅል የሆነ ፈንድ፤በየደረጃ ያሉ የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ-መንግስትና በሌሎች ሕጎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ ጥቅል በጀቱም የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ. ለዳኞችና ከዳኞች ዉጭ ላሉ ሰራተኞች በቂ ደመዎዝና ጥቅማ ጥቅም ለመክፈል የሚያስችል፤

ለ. አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ ማከናወኛ መሳሪያዎችንና አገልግሎቶችን ለመግዛት የሚያስችል፤ እና

ሐ. የካፒታል ዕቃዎችን እና መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት የሚያስችል፤

*3)* የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃ ያሉ የክልል ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎት የሚከፈል የዳኝነት ክፍያ፣ ከቅጣት የሚገኝ ገቢ እና፣ ከለጋሾች የሚገኙ የገንዘብ እና ሌሎች ለፍርድ ቤት የሚከፈሉ ክፍያዎች በየደረጃዉ ላላዉ ለመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ገቢ የሚደረግ ይሆናል ፡፡

*4)* በክልል ም/ቤት አማካይነት ለክልል ፍ/ቤቶች የጸደቀ በጀት በበጀት አርዕስት እና ተመሳሳይ መለኪያዎች ሳይወሰን የውስጥ የበጀት ሽግሽግ መብታቸው ተጠብቆ በዕቅድ ላይ በመመሥረት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ጉዳዮች በነፃነት ከሥራ ላይ ያውሉታል፡፡

## አንቀጽ 33. ስለ ክልል ፍርድ ቤቶች በጀት

1) ክልሉ በሕገ መንግሥቱ ***አንቀጽ 67 (6)*** በተደነገገው መሰረት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ፍ/ቤቶችን በጀት አዘጋጅቶ ለክልል ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

2) የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ከሌሎች የፍርድ ቤት ኃላፊዎች ጋር በመሆን ክልል ምክር ቤት በመቅረብ የበጀት ጥያቄውን ያስረዳል፡፡

3) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለክልል ፍርድ ቤቶች የጸደቀላቸውን በጀት አጠቃቀም አስመልክቶ ለክልል ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

4) የክልል ፍ/ቤቶች የበጀት ዓመት የክልል መንግሥቱ የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 34 ኦዲት**

የክልል ፍርድ ቤቶች የሂሳብ መዝገብና የበጀት አጠቃቀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 መሰረት መከናወኑን በክልል ዋና ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ልዩ ልዩ ደንጋጌዎች**

**አንቀጽ 35. ስለፍርድ ቤቶች ነፃነት**

1. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ከማንኛውም ባለስልጣንም ሆነ ሌላ አካል ነጻ ሆነው የዳኝነት ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡
2. ዳኝነት ሥራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡

**አንቀጽ 36. ተጠያቂነት**

ማንኛውም ዳኛ የሙያው ሥነ-ምግባሩ የማይፈቅድለትን ድርጊት ከፈጸመ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 37. ስለ ይግባኝ**

ማንኛዉም በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ሰዉ አግባብ ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል

**አንቀጽ 38. ደንቦችን የማውጣት ስልጣን**

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችና መመሪያዎችን የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 39. መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍርድ ቤት እና በነባሩ ህግ መስተናገዳቸዉ ይቀጥላል፡፡
2. የአስተዳደር ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ እስከ ሚወጣ ድረስ የሰራተኞች ቅጥር፣ምደባ፣ ዝዉዉር ፣እድገትና አስተዳደር የዚህን አዋጅ መርሆች ሳይቃረን ቀድሞ ሲሰራበት በነበረዉ ህግ መሰረት ይቀጥላል፡፡

## አንቀጽ 40. የተሻሩና ተፈጻሚት የማይኖራቸው ሕጎች

1. የተሸሻለዉ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር **163 / 2011** በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ህግ፣ደንብ፣መመሪያ፣ወይም ውሣኔ በዚህ አዋጅ በተደነገጉት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 41 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በቤኒሻነጉል ጉሙዝ የልሣነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሶሳ፣**

**የካቲት 11 ቀን 2017 ዓ.ም**

**አሻድሊ ሐሰን አልአጀብ**

የቢኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት